# ውርዴ የሚፏልለው

ታሪክ ብልሹ ፣ መዝገባቸው ሲታይ
ገራፊ አስገራፊ ፣ ገዳይና አስገዳይ
ቀድሞ የነበሩ ፣ የወያኔ አገልጋይ
የትላንት ባንዳዎች ፣ የዘንድሮ ታጋይ
ተለዋዋጭ እስስት፣ ዘወተር ወላዋይ
ቃላትን ሞሻሮ ፣ የሰው ልብ አማላይ
ህሊና የሌለው ፣ ዞሮ እንኳን የማያይ
ለነዚህ ቡድኖች ፣ ሆነን ስንቅ አቀባይ
ተጠያቂዎች ነን ፣ ለህዝባችን ስቃይ ።

አስመስሎ አዳሪ ፣ ባድር ባዮች ካባ
ከወያኔ ጋራ ፣ የኖረ ሲጣባ
ከተኮፈሰበት ፣ ከቆመበት አምባ
በወያኔ ሾኬ ፣ ሲጣል በጠረባ
የእምነቱ ውጤት ፣ በሆነ ሰለባ
በምን መመዘኛ ፣ እኛ እናፍስ እንባ
ታጋይ ነው ተብሎ ፣ ከህዝብ ወገን ይግባ ።

ከወያኔ ጋራ ፣ ጮማ እየቆረጡ
ኑሮአቸው የነበር ፣ እየቀላወጡ
በሆነ አጋጣሚ ፣ ተረግጠው ሲወጡ
አጋፍሮ ለማደር ፣ መግቢያ በር ስላጡ
በስደት ዓለም ላይ ፣ ለመኖር ሲመጡ
ተቃዋሚ ሆነው ፣ ዛሬ የሚደመጡ
አሳሪ ገራፊ ፣ የሰው ደም የጠጡ
እነሱ አይደሉም ወይ ፣ የሚበጠብጡ
መንጥሩ ውርዴውን ፣ ከመሃል አስወጡ ።

ዛሬ ስደተኛ ፣ የትላንት ሹመኞች
የወያኔ ሎሌ ፣ አድር ባይ ጥቅመኞች
ህዝብን ያሰለቹ ፣ አርዮስ ግፈኞች
ትግል አዘናጊ ፣ ጥልቅ ብዩ ዝንቦች
እነ በልቶ አይጠግብ ፣ የተራቡ ጅቦች።

የወገኑን ጥቃት ፣ ጥቃቴ የሚለው
ለነጻነት ክብሩ ፣ ጸንቶ የሚታገለው
ስለናት ሃገሩ ፣ ልቡ የቆሰለው
የወያኔ ባናዳ ፣ ውርዴነት የሌለው
ንጹህ ኢትዮጵያዊ ፣ የኛ የምንለው
በሙሉ ልባችን ፣ የምንከተለው
ጠፋ ወይ ባገሩ ፣ ውርዴ የሚፏልለው ።

ታዛቢው

April 13, 2018